የሰ/መ/ቁ. 64813

ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ያሲን አሕመድ መሐመድ አልቀረበም፡፡

**ተጠሪ፡-** ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ባምላኩ አንዳርጌ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በሥር ፍ/ቤቶች የተላለፈበትን የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚል ቅሬታ ስላነሳ ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች የተከሰሰው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675(1) የተመለከተውን በመተላለፍ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሞአል ተብሎ ነው፡፡ ድርጊቱም ብር 10,000(አስር ሺህ ብር) የሚያወጣ ቆርቆሮ ገዝቼ አመጣለሁ በማለት ከግል ተበዳይ ገንዘቡን የወሰዱና ቆርቆሮውን ግን ሳያመጣ መቅረቱን የሚያመለክት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ድርጊቱን አለመፈጸሙን በመግለጽ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ከዚህ በኋላም ክሱን የሰማው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መጀመሪያ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮችን ሰምቶ አመልካች ሊከላከል ይገባል የሚል ብይን ሰጥቶአል፡፡ በመቀጠልም የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃ የሰማ ሲሆን በመጨረሻም አመልካች በዐቃቤ ህግ ክስ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት የፈጸመ መሆኑን አረጋግጫለሁ በማለት የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም የጥፋተኛነት ውሳኔውን እንዳለ በማፅናት በሥር ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን የአንድ ዓመት ከሁለት ወር ጽኑ እስራት ወደሰባት ወር ቀላል እስራት ዝቅ በማድረግ ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ጥር 25 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው አመልካች ዐቃቤ ሕግ (ተጠሪ) ባቀረበበት ክስ መሠረት ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ግራቀኝ ወገኖች ይህን ጭብጥ መሠረት በማድረግ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ በዝርዝር እንዳመለከትነው በዐቃቤ ሕግ ክስ የተመለከተውን ድርጊት አልፈጸምኩም በማለት አመልካች ቢከራከርም፤ ክሱን የሰማው ፍ/ቤት ግን ድርጊቱን ስለመፈጸሙ በማስረጃ አረጋግጦአል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው ፍ/ቤትም እንደዚሁ የተሰማውን ማስረጃ በመመዘን በድርጊቱ መፈጸም እርግጠኛ ሆኖአል፡፡ እንደሚታየው ድርጊቱ ተፈጽሞአል ወይስ አልተፈጸመም የሚለው የፍሬ ነገር ጭብጥ በመሆኑ የሚነጥረው (የሚጣራው) በማስረጃ ነው፡፡ የፍሬ ነገር ጭብጥን በማስረጃ የማጣራት እና የተሰማውን ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን በዚህ መልክ በመምራት መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡ በዐቃቤ ሕግ ክስ የተመለከተው ድርጊት በአመልካች መፈጸሙን በማረጋገጣቸውም ድርጊቱ ከተጠቀሰው የወንጀል ሕጉ ድንጋጌ ጋር አገናዝበው የጥፋተኛነት ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡

በበኩላችንም እንደምናየው አመልካች በዐቃቤ ሕግ ክስ የተመለከተውን ድርጊት ፈጽሞአል ወይስ አልፈጸመም የሚለውን የፍሬ ነገር ጭብጥ የማጣራት ሥልጣን ለሰበር ችሎቱ የተሰጠ ባለመሆኑ በዚህ ደረጃ የምንመረምረው አይደለም፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው እውነታ በክሱ በተጠቀሰው ድንጋጌ የተመለከተውን ወንጀል ያቋቁማል ወይ የሚለው ነጥብ ግን የሕግ ጭብጥ በመሆኑ ተመልክተነዋል፡፡

አመልካች የተከሰሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 675(1) የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፎ ወንጀል ፈጽሞአል ተብሎ እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል፡፡ ድንጋጌው የሚለው

“ማንም ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽናግ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ፣ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ፣ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህን የመሳሰለውን ማናቸውንም አድራጎት የፈጸመ እንደሆነ፣”

ጥፋተኛ ተብሎ በሕጉ የተመለከተውን ቅጣት ይወስንበታል ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች የግል ተበዳይ ለቆርቆሮ መግዣ በማለት የወሰደውን ገንዘብ ወስዶ አስቀርቶአል፡፡ ገንዘቡ ቆርቆሮውን አልገዛበትም ወይም ለሰጠው የግል ተበዳይ አልመለሰም፡፡ ይህ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦበታል፡፡ ገንዘቡን አስካልመለሰ ወይም ለተባለው አገልግሎት ስለማዋሉ እስካላስረዳ ድረስ ደግሞ በድንጋጌው የተመለከተውን ወንጀል ፈጽሞአል ለማለት ነው የሚቻለው፡፡ በሌላ አነጋገር አመልካች የፈጸመው በማስረጃ የተረጋገጠበት ድርጊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675(1) የተመለከተውን ወንጀል የሚያቋቁም ነው፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የምንልበት ምክንያት የለም፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ 102615 ጥር 16 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕግ ሥ/ሥ/ቁ 195(2)(ለ)(2) መሠረት ፀንቶአል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

*ራ/ታ* *የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*